የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 21
ADDIS ABABA-27th January, 2004

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፮/፲፱፻፺፮ ዓ.ም
የገጠር የፋይናንስ አገልግሎትንና ተቋምን ለማሳደግ የሚረዳ ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ............ ገጽ ፪ሺ፭፻፵፪

## CONTENTS

Proclamation No. 386/2004
African Development Fund Loan Agreement for the Rural Finance Intermediation Support Project Ratification Proclamation Page 2542

### አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፮/፲፱፻፺፮

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

የገጠር የፋይናንስ አገልግሎትንና ተቋምን ለማሳደግ የሚረዳ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፳፯ሚሊዮን፩፻፸ሺ ዩ.ኤ. (ሃያ ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባ ሺ ዩኒትስ አፍ አካውንት) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፲፫ ቀን ፪ሺ፫ በቱኒስ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የገጠር የፋይናንስ አገልግሎትንና ተቋምን ለማሳደግ የሚረዳ ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፮/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### PROCLAMATION NO. 386/2004.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

**WHEREAS,** a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provides to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 27,170,000.00 UA (Twenty Seven Million One Hundred Seventy Thousand Units of Account) for financing the Rural Finance Intermediation Support Project, was signed in Tunis, on the 13th day of October, 2003;

**WHEREAS,** The House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Loan Agreement at its session held on the 27th day of January, 2004;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "African Development Fund Loan Agreement for the Rural Finance Intermediation Support Project Ratification Proclamation No. 386/2004."

## ፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. አክቶበር ፲፫ ቀን ፪ሺ፫ በቱኒስ የተፈረመው ቁጥር 2100150007114 የብድር ስምምነት ነው።

## ፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፳፯ሚሊዮን፩፻፸ሺ ዩ.ኤ (ሃያ ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባ ሺ ዩኒትስ አፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



## 2. Definition

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. 2100150007114 signed in Tunis on the 13th day of October 2003 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund.

## 3. Power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 27,170,000.00 UA (Twenty Seven Million One Hundred Seventy Thousand Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 3. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the 27th day of January, 2004

**Done at Addis Ababa, this 27th day of January, 2004**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**